ከአደመ በላቸው

# በዋሺንግተን ነዋሪ ለሆናችሁ ሀገር ወዳዶች ሁሉ አስቸኳይ መልዕክት

ማንነታቸውና የቆየ ሚናቸው ምስጢር ያልሆነው እነ ብርሃኑ ነጋና አጫፋሪዎቻቸው ከሻዕቢያ ጋር በተቀባጀ መልክ አዲስ ሴራ ጎንጉነው ብቅ ብለዋል ። በዋሺንግተን ቻእቢያን አቅፈው የሁለት ቀን ጉባኤ ጠርተዋል። አያያዘውም ከኤርትራ ኮምዩኒቲ ጋር ሆነው ለድምጸ ሻእቢያ ኢሳት ገብዘብ ማዋጫ የኢትዮጵያና ኤርትራ ዘፋኞችንም ጠርተዋል--40 ዶላር ከከፈላችሁ ። የብርሃኑ ተዘራ ( የመለስ አምላኪ) መኖር ባይገርመንን የእነ ፋሲል ደሞዝና ሌሎቹ ደግሞ በሻዕቢያ ድግስ ተሳታፊ መሆናቸው ማሳዘኑ አልቀረም ። ዝርዝራቸውን በኤሳትና ኤካድፍ ድረ ገፅ ታገኙታላችሁ።

ብርሃኑ ነጋ በደርግ ዘመን የአፍሪካ ቀንድ መወያያ ብሎ ወያኔና ሻዕብያን መድረክ ሰጥቶ ኢትዮጵያን ሲያጠቃን ሲያስጠቃ መቆየቱን የዘነጋነው አይደለንም ። አሁንም ይህን ነፍ ሊዘራ ፈልጎ ለሜይ 9 በዋሺንግተን የሁለት ስብሰባ ጠርቷል ። የአነጉ ተማኙች ጌታቸው በጋሻው፤ ሻዕቢያኖቹ አስመሮም ለገሰና ሶፍያ፤ ማርያም ቤት ክርስቲያኑን የሚያምሰው ጌታቸው መታፈሪያና ሚስቱ፤የደርግ ባንዳዎች፤ ወዘተ ሁሉ ተጋብዘዋል ። ብርሃኑ በተሰጠው የኢሳያስ መመሪያ መሰረት ሻዕቢያን ሊያሻሽጥ ተነስቷል ማለት ነው ። ይህን የሻዕቢያ ጉባዔ ሁሉም ኢትዮጵያ አውግዞ በቦታውም መመገኙት የለበትም ። ለሻዕቢያ ድምጽ ለሆነውም ለኢሳትም ገንዘብ መዋጮ ለተባለው ተመሳሳይ ማዕቀብ ማድረግ ተገቢ ነው ። ከሻዕቢያ ጋር በዚህ ተሳታፊ ለመሆን ለተዘጋጁ ዘፋኞችም ውጉዝ ና ከሀዲዎች የሚል መልዕክት ሊደርሳቸው ይገባል ። የብርሃኑ ነጋ ቡድን ራሱን ለሻዕቢያ ሸጧል ። ለኢሳያስ ተገገር ሆኗል ። መወገዝ አለበት፤ ጸረ ኢትዮጵያ ነህ መባል አለበት ። ግንቦት 7 ሆነ ኢሳት የሚለው አብቅቶላቸዋል፤ ጸረ ኢትዮጵያ መሆናቸው ተጋልጧልና በስብሰባውቸውም በዘፈናቸው ንጹህ ኢትዮጵያውያን መገኘት የለባቸውም ። ብርሃኑ እንደ ሻዕቢያ ኢትዮጵያ ማለት ቀፎት የአፍሪካ ቀንድ የሚለው አለምክንያት አይደለም ።

ምን ማድረግ አለብን?

ግንቦት 7 በጠራው ስብሰባ አለመሳተፍ

የግንቦት 7ን አጫፋሪ ምሁር ተብዬዎች ማውገዝ ማጋለጥ

ከግንቦት 7 ሻዕቢያ የዘፈን ምሽት የሚሳተፉትን ዘፋኞች ማውገዝና በላያቸው ላይ ማዕቀብ መጣል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት የሆነውን ሻዕቢያን ሊያሻሻጥ ብርሃኑ ነጋ የሚያካሂደውን እንቅስቃሴ ማውገዝና ማክሸፍ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ከሀዲዎችን እንፋረዳቸዋለን !!